# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 76 ጥቅምት 19 2002 ዓ.ም ገጽ 1


ለምንድነው ወያኔ የአባላቱን ቁጥር ለማብዛት እንዲህ የተንገበገበው? ፍላጎቱ የቁጥር ብዛት ብቻ ከሆነ ለምን የስም ዝርዝር በቀጥታ ከሕዝብ ቆጠራ መዝገብ አይገለብጥም? መልስ ገጽ 3

## ፋሽስቱ መለስ ዜናዊ ለከፍተኛ ህክምና ቤልጂዬም አገር ታክሞ መመለሱ ታወቀ

የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ ባለፈው ማክሰኞ ስርጭቱ እንደዘገበው ከነሃሴ 9 አስከ ነሃሴ 14 ቀን 2001 ዓም በከፍተኛ የአዕምሮና የአንጀት ህመም ስቃይ ቤልጅዬም አገር በብራስልስ ከተማ በሚገኘው የቅዱስ ሉቃስ (ሴንት ሉክ) ሆስፒታል ታክሞ የተመለሰው መለስ ዜናዊ ልክ በሁለት ወሩ ተመልሶ ካለፈው ሳምንት መጨረሻ አስከ ማክሰኞ ጥቅምት 15 ቀን 2002 በተመሳሳይ ሆስፒታል ተኝቶ ስታከም ከቆዬ ቦኋላ ዜናው በተሰራጨበት ምሽት ከሆስፒታል ለቆ ወደ መጣበት መመለሱን ለማወቅ ተችሎአል።

ከወያኔ የደህንነት ክፍል ታማኝ ምንጮች በተገኘ መረጃ መሰረት መለስ ዜናዊን አጅበው ወደ ቤልጅዬም ከተላኩት 8 ሰዎች 5ቱ የጥበቃ ጋዶች ሲሆኑ በብሄር ተዋጾአቸውም በምግብ ቀማሽነት እንዲከተለው ከተደረገ ከበደ ይታፈሩ ከተባለ የአማራ ተወላጅ በስተቀር ሁሉም የትግራይ ተወላጆች ነበሩ ። ስማቸውም ፤

1ኛ. ገብረትንሳዔ ተስፋዬ የጥበቃ ቡድኑ ሃላፊ የያዘው መሳሪያ ቁጥር 36302480 ከ14 ጥይቶች ጋር
2ኛ. አብረሃ ገድሉ፡ የጥበቃ አባል የያዘው መሳሪያ ቁጥር 36302466 ከ28 ጥይቶች ጋር
3ኛ. ሃይሉ ገብረመድህን የጥበቃ አባል የያዘው መሳሪያ ቁጥር 36302465 ከ28 ጥይቶች ጋር
4ኛ. ገብረመድህን ገብረመስቀል የጥበቃ አባል የያዘው መሳሪያ ቁጥር 36302495 ከ28 ጥይቶች ጋር
5ኛ. ተስፋሚካኤል አበበ የጥበቃ አባል የያዘው መሳሪያ ቁጥር 36302500 ከ28 ጥይቶች ጋር ሲሆኑ ገብረትንሳኤ ገብረሚካኤል የተባለው የመለስ ዜናዊ ልዩ ረዳትና የግል ሃኪሙ ዶ/ር ወልደገብርኤል ኔርአ የተባሉት አጅበውት ተጉዘው እንደነበር ታውቆአል። **ወደ ገጽ 4 ዞሯል**

## ህዝቡ ለወያኔ የምርጫ ፕሮፓጋንዳ ቁብ እንዳልሰጠው ተዘገበ

መጪውን የይስሙላ ምርጫ በተመለከተ በወያኔ የመገናኛ ብዙሀን ተደጋግሞ ለሚቀርበው ቅስቀሳ ህዝቡ ቁብ እንዳልሰጠው ተገለጸ

ዘጋቢያችን በአዲስ አበባ ከተማ ተዘዋውሮ ያነጋገራቸው ሰዎች እንደገለጹት፣ ከምርጫ 97 በሁዋላ ህዝቡ በምርጫ ላይ ያለው እምነቱ ሙሉ በሙሉ ተሸርሽሮአል።

አንድ ስማቸው እንዳይነገር የጠየቁ የአዲስ አባባ ነዋሪ “ወያኔ በግንቦት 97 ምርጫ ማግስት በአጋዚ ጥይት ላለቁት ወጣቶች ሀላፊነቱን ወስዶ ካሳ ሳይከፍል እንደገና ስለምርጫ ማውራት አይጥመኝም” ብለዋል።

አቶ ታከለ የተባሉ ነዋሪ በበኩላቸው በወያኔ ዘመን ነጻ ምርጫ ይደረጋል ብለው ፈጽሞ እንደማያምኑ ተናግረው፣ በወያኔ መገናኛ ብዙሀን የሚደረገው ቅስቀሳ የህዝቡን የተዳፈነ የቁጭት እሳት ከመቀስቀስ በተረፈ ሌላ ፋይዳ የለውም ሲሉ ተናግረዋል። አቶ ታከለ በአካባቢያቸው የሚገኙት የወያኔ ካድሬዎች የቀበሌአቸውን ህዝብ ለምርጫ እንዲቀሰቅሱ እንደጠየቋቸው ተናግረው፣ እርሳቸው ግን በምርጫው ተስፋ በማጣታቸው መልስ አለመስጠታቸውን ገልጸዋል። **ወደ ገጽ 4 ዞሯል**

## በኢትዮጵያ የተከሰተው ረሀብ ከፍተኛ እልቂት ሊያስከትል እንደሚችል አንድ የእንግሊዝ ባለስልጣን አስጠነቀቁ፣ ወያኔ የተራበውን ህዝብ ቁጥር በትክክል እንዲያስታወቅ ጠየቁ

በእንግሊዝ የአለማቀፍ የልማት ሚኒስትር የሆኑት ሚስተር ዳግላስ አሌክሳንደር ለአገራቸው የፓርላማ አባላት በጻፉት ደብዳቤ ላይ እንደገለጹት፣ የዘንድሮው ሰብል ውጤት ካላማረ፣ ከ25 አመታት በፊት ተከስቶ የነበረውን አይነት አስከፊ ረሀብ በኢትዮጵያም በያዝነውም አመት ይደገማል ሲሉ አስጠንቀዋል። ሚስተር አሌክሳንደር የረሀቡ መንስኤ በሰው ሰራሽና በተፈጥሮ መዛባት ምክንያት የመጣ መሆኑን ተናግረው፣ የወያኔ አገዛዝ የረሀብተኛውን ቁጥር ከሚደብቅ ይልቅ ትክክለኛውን ቁጥር እንዲያወጣም ጠይቀዋል። በተለይ ለረጅም ጊዜ ጦርነት በሚካሄድበት የሶማሊ ክልል የእርዳታ ድርጅቶች ተዘዋውረው እርዳታ ለመስጠት አለመቻላቸው በእጅጉ እንዳሳሰባቸው የገለጹት ሚኒስትሩ፣ የወያኔ አገዛዝ ክልሉን ለእርዳታ ድርጅቶች ክፍት ማድረግ እንዳለበትም ተናግረዋል።

ከሶስት አመት በፊት የይስሙላው ፕሬዚዳንት ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ ለአሻንጉሊቶቹ የፓርላማ አባላት “የኢትዮጵያ ህዝብ በ1999ዓም በምግብ ራሱን ይችላል” ብሎ መናገሩን ተከትሎ የአለማቀፍ የእርዳታ ድርጅቶችና የአለማቀፍ መንግስታት ለአምባገነኑ የመለስ አገዛዝ ያላቸውን አድናቆት ሲገልጹ እንደነበር የሚታወስ ሲሆን፣ የመለስ አገዛዝም በወቅቱ አቅርቦት የነበረውን የውሸት ሪፖርት ለመሸፋፈን የተረጅውን **ወደ ገጽ 4 ዞሯል**

## 2ሺ የዩኒቨርስቲ መምህራን የአለም አቀፍ ቋንቋ መመዘኛ ፈተና ወደቁ

ከተለያዩ ዩኒቨርስቲዎች ተውጣጠው የአለማቀፍ የእንግሊዝኛ ችሎታ መመዘኛ ፈተና በእንግሊዝኛው አጠራር ኢንተርናሽናል ኢንግሊሽ ላንጉዊጅ ቴስቲንግ ሲስተም የወሰዱ ከ2 ሺ በላይ መምህራን መውደቃቸው እንደተሰማ፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሰቲ የቋንቋ ዲፓርትመንት ለመምህራኑ የእንግሊዝኛ ትምህርት ስልጠና ለመስጠት እየተዘጋጀ ነው። መምህራኑ ፈተናውን የወሰዱት በውጭ አገር ዩኒቨርስቲዎች በመሄድ የማስተርስና የፒኤች ዲ ዲግሪ ትምህርታቸውን ለመቀጠል እንዲያስችላቸው ቢሆንም፣ ፈተናውን የወሰዱት 2ሺ መምህራን በሙሉ የማለፊያ ነጥብ ለማግኘት ባለመቻላቸው ትመህርታቸውን በውጭ አገራት ዩኒቨርስቲዎች ሂደው ለመከታተል ሳይችሉ ቀርተዋል።

የመምህራኑ መውደቅ በአገሪቱ ያለውን የትምህርት ፖሊሲ ጥራት ችግር ያሳያል ያሉት በትምህርት ሚኒስቴር መስሪያቤት ውስጥ የሚሰሩ አንድ ከፍተኛ ኤክስፐርት፣ በእነዚህ መምህራን የሰለጠኑ ተማሪዎች የባህሪ ለውጥ አምጥተው አገራቸውንና ህዝባቸውን ለመለወጥ የሚያስችላቸውን እውቀት ጨብጠው ይመረቃሉ ማለት ፈጽሞ የማይታሰብ ነው ሲሉም በቁጭት ተናግረዋል።

ለፖለቲካ ፍጆታ ተብሎ፣ ያለ ጥናትና ያለበቂ መምህራን፣ በተለያዩ አካባቢዎች የተገነቡት ዩኒቨርሰቲዎች የሚያስመርቁዋቸው **ወደ ገጽ 4 ዞሯል**

## ህወሀት ለዘመናት የኢትዮጵአውያን የገቢ ምንጭ በመሆን ሲያገለግል የቆየውን የቡና ገበያ ቀስ በቀስ በቁጥጥሩ ስር እያስገባው መምጣቱን አንድ ታዋቂ የዜና ምንጭ ገለጸ

ብሉምበርግ ኒውስ ሰሞኑን ባወጣው ዘገባ ላይ እንደገለጸው ለትግራይ ልማት ተብሎ የተቋቋመው ጉና የንግድ ድርጅት ወደውጭ የሚላከውን የአገሪቱን የቡና ገበያ ሙሉ በሙሉ በቁጥጥሩ ስር እያስገባ ነው። ጉና ና ሌሎች የህወሀት ኩባንያዎች ለዘመናት የኢትዮጵያውያን የኢኮኖሚ ዋልታ ሆኖ ሲያገለግል የቆየውን የቡና ገበያ ለመቆጣጠር የበቁት፣ በዚሁ ስራ ተሰማርተው የነበሩትን የግል የቡና ላኪ ድርጅቶችን በመዝጋትና ባለንብረቶችንም በማሰር መሆኑን ብሉምበርግ ዘግቧል።

ህወሀት በቅርቡ ታዋቂ የሆኑ የግል የቡና ላኪዎችን መወንጀሉንና ከገበያ እንዲወጡ ማድረጉን መዘገባችን የሚታወስ ሲሆን፣ ይህን ያደረገውም የቡናውን ገበያ ሙሉ በሙሉ ለአንድ ክልል ጠቀሜታ ተብሎ በተቋቋመው ጉና የንግድ ድርጅት ስር በማድረግ የዘረፋ ተግባሩን ለማጠናከር መሆኑን በተደጋጋሚ ስንገልጽ መቆየታችን ይታወሳል።

በአንድ ወቅት ተርቦ በነበረው የትግራይ ህዝብ ስም በተሰበሰበ የውጭ እርዳታ ገንዘብ የተቋቋመው ጉና የንግድ ድርጅት አሁን ደግሞ አገሪቱን ሀብት በመዝረፍ ስራ ላይ መሰማራቱ ብዙዎችን እያበሳጨ ነው።

## ከ500 በላይ አዲስ የኮሌጅ ምሩቃን በታክስና በጉምሩክ መስሪያቤቶች ሊቀጠሩ ነው። አብዛኞቹ የትግራይ ተወላጆች ሲሆኑ፣ ጥቂቶቹ ደግሞ የወያኔ አባላት የሆኑ ተማሪዎች ናቸው

አዲስ አበባ የሚገኘው ወኪላችን እንደገለጸው የወያኔ አባል የሆኑና ከተለያዩ ኮሌጆች የተውጣጡ 500 ተማሪዎች በሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ ውስጥ ስልጠና እየተሰጣቸው ነው። ሰልጣኞቹ በተለያዩ ኮሌጆች የወያኔ አባል ሆነው ሲያገለግሉ መቆየታቸውን የገለጸው ወኪላችን፣ በምዝገባ ወቅት በካምፓስ ቆይታችሁ ያደረጋችሁትን የፖለቲካ አስተዋጽኦ ጻፉ ተብለው መጠየቃቸውንና በዚህም መሰረት መመረጣቸውን ሰልጣኞችን እንደነገሩት ዘግቧል። አብዛኞቹ ሰልጣኞች በታክስ ቢሮዎችና በጉምሩክ መስሪያቤቶች የሚቀጠሩ ሲሆን፣ በብሄር ተዋጽኦም ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የትግራይ ብሄር ተወላጆች መሆናቸውን ማረጋገጥ መቻሉን ዘግቧል።

ሰልጣኞቹ ለሁለት ወራት በሚቆዩበት ጊዜ የፖለቲካ ስልጠና ብቻ የሚሰጣቸው ሲሆን፣ በሚመደቡባቸው መስሪያቤቶችም የወያኔ ወከሎች በመሆን እንደሚያገለግሉ ዘገባው አስረድቷል።

ወያኔ በ “ወይ’ን ለኑሮ” ፖሊሲው የመንግስት መስሪያ ቤት ሰራተኞችን በራሱ አባለት እየተካ እንደሚገኝ በተደጋጋሚ መዘገቡ ይታወሳል።

# “ወይን ለመኖር” የት ያደርሰናል?

ለመኖር ብሎ የወያኔ አባልነት ፎርም መሙላት “ወይን ለመኖር” የሚል ስያሜ አግኝቷል። ስታሊናዊ ሁሉን ጠቅላይ አገዛዝ፤ “እንድዘርፍ አግዘኝ፤ አለበዚያ አጠፋሃለሁ” ዓይነቱ የማፍያ አሠራርና ግብር በማብላት የመኮፈስ ፊውዳላዊ ባህል ሲዳቀሉ “ወይን ለመኖርን” ፈጠሩ። “ወይን ለመኖር” ያልተፃፈ ነገር ግን ከተፃፈው በላይ በመተግበረ ላይ ያለ የወያኔ ህገ-መንግሥት ነው። ስለሆነም “ከወይን ለመኖር” ጋር የማይጣጣሙ አዋጆችና ደንቦች ሥራ ላይ አይውሉም።

ተጽፎ ያለው መመሪያ ምንም ይሁን ምን በገጠር ያለው አርሶ አደር ቁራጭ የእርሻ መሬት፣ የግብርና ባለሙያዎች የምክር እገዛ፣ የማዳበሪያና ዘር ግዢ፣ ብድር ወይም እርዳታ ለማግኘት መወየን ይኖርበታል። በከተሞች ውስጥም ሥራ ለመቀጠር፣ ለደረጃ እድገት፣ ለከፍተኛ ትምህርት እድል መወየን አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታ ነው:: በንግዱም ዘርፍ የሥራ ቦታ ለማግኘት፣ የመንግሥት ጨረታዎችን ለማሸነፍ፣ የባንክ ብድር ለማግኘት፣ ከጉምሩክ እቃ ለማስለቀቅ፣ የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት መወየን ግድ ነው። በገጠር ለልማት ስብሰባ የወጡ አርሶ አደሮች በስብሰባው መጨረሻ የአንዱ ወያኔ ቅርንጫፍ አባል መደረጋቸው ይነገራቸዋል። መምህራንና ሌሎች የመንግሥት ሠራተኞች ለቢ.ፒ.አር ተብለው ይሰበሰቡና ካልወየኑ በስተቀር በአዲሱ አሠራር ቦታ እንደማኖራቸው እንዲያውቁት ይደረጋል። እነ መለስና ስብሃት በእንዲህ ዓይነት መንገድ ያጠራቀሙትን አባል ደማምረው ሰባት ሆነን የጀመርነውን ድርጅት በቅርቡ ሰባት ሚሊዮን እናደርሰዋለን ብለው ይፎክራሉ።

ለምንድነው ወያኔ የአባላቱን ቁጥር ለማብዛት እንዲህ የተንገበገበው? ፍላጎቱ የቁጥር ብዛት ብቻ ከሆነ ለምን የስም ዝርዝር በቀጥታ ከሕዝብ ቆጠራ መዝገብ አይገለብጥም?

አባላትን በግዴታም ሆነ በማባበል መመዝገብ ወዳጆችን ማፍራት ማለት አለመሆኑን የወያኔ መሪዎች ያጡታል ብሎ መገመት የዋህነት ነው። የደርጉ ኢሠፓ እጣ ፈንታ በአይናቸው ያዩት ነገር ነውና የቆሙበት መሠረት ሲናጋ የገነቡት ድርጅት እንደሚፈራርስም የሚያጡት አይመስልም። ታድያ ከዚህ ጅምላ የአባልነት ምልመላ ጀርባ ምን የተደበቀ ሸር አለ? የዚህ ምላሽ በመግቢያው ላይ ባጭሩ ቀርቧል። በመጠኑም ቢሆን ዘርዘር አድርገን እንመልከታቸው::

### 1. ሁሉን ጠቅላይ አገዛዝን ማስፈን

ወያኔ እየገነባው ያለው አገዛዝ ስታሊን ለ30 ዓመታት ሶቭየት ኅብረትን፤ ኤንቨር ሆዣ ለ40 ዓመታት አልባኒያን ጠፍረው የገዙበት ስልት ነው። በዚህ የአገዛዝ ስልት መሠረት በፓርቲና መንግሥት መካከል ልዩነት የለም። የሁለቱም ዋና ሥራ ዜጎችን መቆጣጠር ነው። ለቁጥጥር እንዲያመች ደግሞ እያንዳንዱ ሰው በመዋቅር መያዝ አለበት። የሚሸመደድ ድጋም እንጂ የሚታሰብ አዲስ ነገር የለውምና የአመለካከትና የርዕዮተዓለም ጉዳይ እጅግም የሚያሳስብ አይደለም። ዋናው መመዝገብና በመዋቅር መታቀፍ ነው።

የወያኔዋ ኢትዮጵያ ሞዴል የኤንቨር ሆዣዋ አልባኒያ ስለመሆኗ በርካታ ማስረጃዎችን ማቅረብ ቢቻልም አንዱን ብቻ አንስተን እንለፍ። ወያኔ እስከ 2002 ምርጫ ድረስ ስድሳ በመቶ የትግራይ ክልል ነዋሪን አባል የማድረግ እቅድ ነድፏል። የተባለው ጊዜ የተቃረበ በመሆኑ ይሄኔ እቅዱ ሙሉ በሙሉ ተሳክቶ ሊሆን ይችላል። ለምን 60% ተመረጠ? መልሱ 40%ው ነዋሪ ገና “ለአቅመ ፓርቲ” ስላልደረሰ!!! በወያኔ እሳቤ እድሜው የደረሰ ትግሬ በሙሉ የወያኔ አባል መሆን አለበት። አለበለዚያ ለነፍጠኞች ያደረ ከሃዲ ነው። ይህ ስዕል የትግራይ ሕዝብ በእንዴት ያለ አፈና ውስጥ እንዳለ ያሳያል። ይህ በትግራይ ላይ ጎልቶ ይታይ እንጂ የመላዋ ኢትዮጵያ ሃቅ ነው። የወያኔ ህልም ሁሉንም ዜጋ በፓርቲ መዋቅር ውስጥ አስገብቶ ጠፍሮ አስሮ መግዛት ነው።

ሕዝብን በድርጅት አባልነት ስም በመዋቅር ማስገባት ለአንባገነኖች የሚሰጠው ዋነኛ ጥቅም የማኅበረሰብን ስነልቦና መስበሩ ነው። ዜጎች የአምባገነኑን መንግሥት ኃይል በመጠን በላይ አግዝፈው፤ የራሳቸውን ደግሞ አንኳሰው እንዲመለከቱ ያደርጋቸዋል። “መንግሥት እያንዳንዱን ነገር አብጠርጥሮ ያውቃል” በሚል የፍራቻ ቆፈን ተይዘው እንኳንስ በተግባር መቃወም ማሰብን እንኳን እንዲፈሩ ያደርጋቸዋል። እያንዳንዱ ሰው ጓደኛውን እንዲጠረጥር በማድረግ የአምባገነኖች የስለላ ተቋም ጠንካራና ሁሉን አዋቂ እንዲመስል ያደርጉታል።

ሁሉን ጠቅላይ አገዛዝ ወያኔን በእጅጉ ጠቅሞታል። የወያኔ የጦር ሠራዊትና የስለላ ተቋም ደካሞች ናቸው። እነዚህ ሁለቱ ተቋማት እንዳሁን ተዳክመው አያውቁም። የወያኔ ስለላ ለምሳሌ በመሃይም ጀሮ ጠቢዎች የተሞላ፤ በቀላሉ የሚታለሉ፤ ዓይናቸው ሥር የሚሠራውን እንኳን ማየት የማይችሉ ድውያን ናቸው። ቀላል ማስረጃ ለመስጠት ዓይኖቻቸውን ባፈጠጡበት ወህኒ ቤት ውስጥ መጽሃፍ ተጽፎበት ሲወጣ፣ ሲታተም፣ ከተማ ሲሸጥ አላዩም፤ አልሰሙም። ብዙ ሰው በወያኔ መዋቅር መያዙ ሕዝብ ልብ ውስጥ የዘራው ፍርሃት እነዚህ ተቋማት የሌላቸውን ግዝፈት ያላቸው እንዲመስል አድርጓል።

### “እንድዘርፍ አግዘኝ፤ አለበዚያ ግን አጠፋሃለሁ”

ስታሊንና ኤንቨር ሆዣ በፋሺስታዊ ጭካኔያቸውና በሁሉን ጠቅላይ አምባነን ሥርዓታቸው የሚጠሉ ቢሆንም ተራ ወንበዴዎች ግን አልነበሩም፤ የአገራቸውና መንግሥታቸው ክብር በማዋረድም አይታሙም። ወያኔ ግን ኢትዮጵያን በመጥላት ያደጉ ግለሰቦች ቡድን ነው። እነዚህ ግለሰቦች ሲዘርፉም ሆነ ሲዋሹ ለከት የላቸውም። ወያኔ የሚያካሂደው መጠነ ሰፊ ዝርፊያ ያለ ብዙ ኢትዮጵያዊያን ትብብር በጥቂት የወያኔ ግንባር ቀደም አባላት ብቻ ሊከናወን ፈጽሞ ባልቻለም ነበር። እናም ለኑሮ ብሎ ወያኔን የተቀላቀለ ከሚከተሉት ቢያንስ በአንዱ መንገድ መተባበሩ አይቀርም።

#### 1.1 በዝርፊያ መተባበር

ኢትዮጵያዊያን ለትናንሽ ጥቅሞች ብለው የወያኔ አባል በሆኑ መጠን ወያኔ የዝርፊያውን አድማስ ያሰፋል። “የአባትህ ቤት ሲዘረፍ አብረህ ዝረፍ” የሚሉ ሰዎች መኖራቸው ወያኔን ጠቅሞታል። በትንሹ እንኳን የጥቅም ተካፋይ የሆነ ሰው ትልቁን ዘረፋ የመቃወም ድፍረት ያጣል። በዚህ የተበረታታው የወያኔ ዘረፋ እየሰፋ መጥቶ እነሆ የእርሻ መሬቶችን ለባእዳን እስከ መሸጥ ደርሷል። አንድ ኢትዮጵያዊ በወያኔ አባልነቱ የሚያገኘው ጥቅም ራሱን ለባርነት የሸጠበት ዋጋ አድርጎ ቢያየው ይመረጣል።

#### 1.2 በዝምታ መተባበር

ፍርሃት በፈጠረው የአቅመ ቢስነት ስሜት ወይም ከዚህ በፊት የተደረጉት ጥረቶች ባለመሳካታቸው ሳቢያ የተፈጠረው ደንታ ቢስነት “ለወይን ለመኖር” መስፋፋት ተጨማሪ ምክንያቶች ሆነዋል። ቁጥራቸው ጥቂት ያልሆነ ኢትዮጵያዊያን ልባቸው ከግንቦት7 ጋር ቢሆንም ፍርሃታቸው ከወያኔ ጋር አሰልፏቸዋል።

### 2. ፊውዳላዊ መኮፈስ

ግብር ማብላት የኢትዮጵያ ፊውዳል ባህል ነው። ሀዲስ ዓለማየሁ “በፍቅር እስከ መቃብር” በበዛብህ አንደበት እንደተናገሩት የመኳንንት ግብር ግብዣ ሳይሆን ሰው ለቁራጭ እንጀራ ራሱን አዋርዶ፣ ተገፍትሮ፣ ተደብድቦ፣ የማይበላ በልቶ ተገዢነቱን በተግባር የሚገለጽበት፤ መኳንንቱም ይህንን እያዩ የሚደሰቱበት ሥርዓት ነው።

ወያኔ ይህንን የቆየ የፊውዳል ባህል አዲስ ቀለም ሰጥቶታል። የወያኔ አባል በመሆን ለሚገኝ ትንሽ ጥቅም ብዙዎች ክብራቸውን አሳልፈው ሲሰጡ፤ በየግምገማው ስድብን እንደ ምርቃት ሲቀበሉ የወያኔ መኳንንት ሃሴትን ያደርጋሉ። “ተራሮችን ስላንቀጠቀጠው” ትግላቸው በየጊዜው አዳዲስ ነገር እየጨማመሩበት ይደሰኩራሉ።

### “ወይን ለመኖርን” ለማጥፋት ምን ማድረግ እንችላለን?

1. ከሁሉ አስቀድሞ ለራሳችን ክብር እንስጥ፤ ለጥቅም ወይም በፍርሃት ምክንያት የወያኔ አባልነት ፎርም በመሙላት ባርነትን አንቀበል።
2. እኛ የምናልማት ኢትዮጵያ ለጥቅም ሲሉ ወይም በፍርሃት ነፃነታቸውን አሳልፈው በሚሰጡ ሰዎች መገንባት አትችልም። እንቢ ለወያኔ ያሉ ወገኖቻችን የተጎናፀፉትንና ወደፊትም የሚኖራቸው ክብር፤ ከማይቀረው የወያኔ ውድቀት በኋላ ተባባሪዎቹ የሚደርስባቸው ውርደት ጋር በማወዳደር ለልባችን ልብ እንስጥ።
3. ከሁሉ አስቀድሞ ማሸነፍ የሚኖርብን በውስጣችን ያለውን ፍርሃት ነው። የወያኔ ሠራዊት ምን ያህል ደካማ እንደሆነ ሶማሊያና ኦጋዴን አሳይተውናል፤ አንበሳ የሚመስለው በሚፈራበት ቦታ ብቻ ነው። የስለላ ተቋሙ ጥቂት ዘረኞች የተሰባሰቡበት የማይማን ጎተራ ነው። አባላቱ አስተሳሰባቸው ትንሽ፤ ብቃታቸው ዝቅተኛ ነው። እነዚህ ኃይሎች ሁሉን ነገር የተቆጣጠሩት አድርጎ ማሰብ ራስን ማዋረድ ነው። ስለዚህም መሸሽ ሳይሆን በየጊዜው ልንፈታተናቸው፣ ልንጎነታትላቸውና ልንፋለማቸው ይገባል።
4. የነጻነት ኋይሎች መዋቅራቸውን ማስፋትና በርካታ ህዋሶችን መፍጠር እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው። የወያኔን የመዋቅር ስፋት በነፃነት ኃይሎች የመዋቅር ስፋት መጋፈጥ መቻል አለብን። ህዋሶቻችንን በሁሉም ቦታና ባልተማከለ አደረጃጀት ጭምር በብዛት በመመስረት አገራችን የእኛ መሆኗን ለሕዝባችን ማሳየት አለብን።
5. በማናቸውም ምክንያት ራሳቸውን ወያኔ ጉያ ውስጥ ያገኙ የሕዝብ ወገኖች ካሁን በኋላ መሥራት ያለባቸው ወያኔን ከውስጥ ሆኖ የማፍረስን ሥራ ነው።

“ወይን ለመኖር” የኢትዮጵያን ሕዝብ ያዋረደ፤ ለትውልድ የሚተርፍ የማኅበራዊ ስነልቦና ኪሳራ የሚያደርስ፤ ደካማውን ወያኔን ጠንካራ በማስመሰል የሕዝባችንን የትግል ሃሞት የሚያፈስ በመሆኑ ሁላችንም አጥብቀን ልንዋጋው ይገባል።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

ማስታወቂ

የግንቦት 7 ድምጽ የአድማጮቹን አስተያየት በስልክ ጭምር ለመቀበል እንዲያስችለው አንድ የስልክ መስመር ከፍቶአል ። ስለዚህ ስለፕሮግራማችን አስተያየት ሲኖራችሁ በስልክ ቁጥር 0044- 203-286- 9661 ልትደውሉልን የምትችሉ መሆኑን እንገልጻለን።



የፖስታሳጥን ቁጥር ፦ POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

# መራብ የማይገባው ሕዝብ ሲራብ ክፍል 1

## ሀ) የዘመነ ህዳሴው ድርቅ

ድርቅ ኢትዮጵያን እያጠቃ ነው፡፡ ይህ የተፈጥሮ ክስተት ለአገራችን አዲስ አይደለም፡፡ የሰሜኑ የአገራችን ክፍል ለዚህ አደጋ ለብዙ አመታት ተጋልጧዋል፡፡ በዚህ አካባቢ ያለው መሬት እረፍት አግኝቶ እራሱን ለማደስና ለማገገም እድል ሳያገኝ ለዘመናት ሲታረስ የነበር በመሆኑ የአፈሩ ልማት ተሟጧል፡፡ በየጊዜው እየጨመረ የሄደው የህዝብ ብዛት፤ በጭቆናና በዘረፋ ላይ የተገነባው የፖለቲካና የማህበራዊ ባህሎቻችን ከአየር ንብረታችን ባህርይ መለዋወጥ ጋር ተዳምረው ችግሩን አባብሰውታል፡፡ አካባቢው በገዥና አልገዛም ባይ መካከል ይደረግ የነበር ያልተቋረጠ የሥልጣን ሽኩቻ አውድማ እንደመሆኑ ህዝቡም እንደመሬቱ የተራቆተ ነው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በህዝብ ብዛት ምክንያት ጫካው ለእርሻና ለማገዶ እየተመነጠረ መሬቱ ለጎርፍና ለነፋስ ተጋልጦ አፈሩ እየታጠበ ወደጎረቤት አገሮች በመጓዙ የመሬቱ ልማት እየመነመነ፤ አፈር አልባነት እያደገ፤ አካባቢው ወደ ድንጋይነት ተለውጧል፡፡ አማራጭ ያልነበረው ሕዝብ ልፋቱና ድካሙ እያደገ ቢሄድም ምርቱ ግን እየተመናመነ ጠግቦ ማደር ብርቁ ሆነ፡፡

ጠግቦ ቢበላም የተበላው ሆድ ከመሙላት አልፎ ለሰውነት እድገትና ለአዕምሮ ልማት አስፈላጊ የሆኑ ንጥረ-ነገሮች በብቃት ስለማያካትት አካሉ ከመክሳት ፊቱ ከመጠውለግና አቅመቢስ ከመሆን አልዳነም፡፡

የሰሜኑና የምስራቁ የአገራችን ክልሎች ለዚህ መሰል የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች ዘለግ ላሉ ጊዜያት ሲጋለጡ፣ ቆላነትና ብሎም በረሃነት ወደ ሌሎች አካባቢዎች እየተዛመተ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በደን የተሸፈኑ፤ ልማትና ምርታማነታቸው ከፍተኛ የነበረው የደቡብ ኢትዮጵያ አካባቢዎች ለተመሳሳይ ክስተት ተጋልጠዋል፡፡

ድርቅ ለምን አጠቃን አንልም፡፡ አገራችንን በተደጋጋሚ ሲያጠቃ የነበረ፤ ወደፊትም ሊያጋጥም የሚችል የተፈጥሮ ክስተት በመሆኑ፡፡ ድርቅ የጂኦግራፊ፤ የአየር ባህርይና፤ ከኛ ቁጥጥርና ምናልባትም ከእኛ እውቀት ውጪ የሆኑ ኃይሎች ውጤት በመሆኑ፡፡

የድርቅን መከሰት የመቀበላችንን ያህል እሱን ተከትሎ የሚደርሱ አደጋዎችና ጉዳቶችን ግን በፍፁም የማይታሰቡ መሆን ነበረባቸው፡፡ እንደ እድል ሆኖ ከታሪካችን ባለመማራችን፤ ተምረንም አስፈላጊውን ዝግጅት ባለማድረጋችን የ1966ቱና የ1977 እልቂትና ሰቆቃ ራሱን ሊደግም እየተዘጋጀ ነው፡፡

እኛ የጉዳዩ ባለቤቶች ዝም ብለን ሌሎች ለኛ የሚጮሁበት ደረጃና ዘመን ደርሰናል፡፡ ተፈጥሮ ጨክኖብን፤ ወገንም እንዳይረዳዳ ይህ እኩይ መንግስት ነኝ ባይ ቡድን ማእቀብ ጥሎብናል፡፡ የቀረን ወደ ፈጣሪና ወደ አለም አቤቱታ ማቅረብ ብቻ ሆንዋል፡፡

ይህን በራስ ላይ የምንሰነዝረውን ትዝብትና ቁጣ ለጊዜው ወደዳር አድርገን ድርቁ እያደረሰና በአስቸኳይ ካልተገታ ሊያደርስ የሚችለውን ከፍተኛ አደጋ እናስብ፡፡

ከዚህም ዘለቅ ብለንም የወያኔ አገዛዝ ጥርሱን አግጦ የመጣውን አደጋ ለመመለስ ምን እያደረገ ነው? የአለም ሕብረተሰብስ ምን እያደረገ ነው? እኛስ ምን እያደረግን ነው? የሚሉትንና ተዛማጅ ጉዳዮችን አጠር አጠር አድርገን እንመልከት፡፡

አፍጦ የመጣውን ችግርና የሚከተለውን አደጋ መገመት አስቸጋሪ አይደለም፡፡ ይህን ባጭሩ ልንገልፅ እንችላለን፡፡ በአሁኑ ጊዜ ድርቅ በከፍተኛ ደረጃ አገሩን እያጠቃ ነው፡፡ በብዙ የአገራችን ክልሎች የመኸር ምርት አዝመሚያው የሚያወላዳ አይደለም፡፡ ትልቅ አደጋ ሊከሰት ይችላል፤ ብዙ ህዝብ ሊያልቅ ይችላል፡፡ ይህ ዜና አዲስ አይደለም፤ በአለም ናኝቷል፡፡

## ለ) የጥቃት ሰለባ

በዘንድሮው ድርቅ እየተጠቃ ያለው ሕዝብና የቆዳ ስፋት ቀደም ሲል ከነበሩት እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡ በተባበሩት መንግስታት የአስቸኳይ እርዳታ ማስተባበሪያ ቢሮ ባወጠው ዘገባና ካርታ መሠረት ለድርቅ አደጋ በአንፃራዊ መልኩ ያልተጋለጡት እጅግ የተወሰኑ ሲሆን እነዚህም በሰሜንና ምዕራብ አካባቢዎች ያሉት ትግራይ፤ ቡኔሻንጉል ጉሙዝ፤ ወለጋና ምዕራብ ሸዋ ናቸው፡፡

ባንፃሩ ድርቁ እጅግ በጣም የበረታባቸውና ከፍተኛ አደጋ እየደረሰባቸው ያሉት በኢትዮጵያ ሶማሌ፤ በደቡብ ኦሮሚያ (ቦረና)ና ደቡባዊው የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ነው፡፡

በጎንደር፤ በጎጃም፤ በምስራቅ ኦሮሚያ (አርሲና ባሌ)፤ በጋምቤላና በደቡብ ብሄር ብሁረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በድርቅ ምክንያት አብዛኛው ምርት ቢከስምም ያደረሰባቸው ወይም ሊያደርስ የሚችለው ጉዳት ገና ተለይቶ አልታወቀም፡፡ ሆኖም በነዚህ አካባቢዎች አደጋውን ለመከላከልም ሆነ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት ለማምከን እርዳታ አስፈላጊ መሆኑ ግንዛቤ ላይ ተደርሷል፡፡

ይህን ካርታ ይዘን ለአደጋ የተጋለጠውን ሕዝብ ስናሰላ ቁጥሩ ከአጠቃላይ ሕዝብ ከግማሽ የሚበልጥ ሆኖ ይገኛል፡፡ በአደጋው መጠን ተለይቶ ሲታይም ለከፍተኛ አደጋ የተጋለጠው ሕዝብ ወደ 20 ሚሊዮን ይገመታል፡፡ ድርቁ እስከአሁን አስከፊ ደረጃ ላይ አልደረሰም ተብሎ በታሰበባቸው አካባቢዎች ከሚኖረው ህዝብ መሃል ወደ 25 ሚሊዮን የሚጠጋው እርዳታ እንደሚያስፈልገው ተገምቷል፡፡ ሲጠቃለል ለጉዳት የተጋለጠው ሕዝብ ወደ 45 ሚሊዮን ይገመታል፡፡

ይህ ግምት ችግሩ ያልታወቀለትን የከተማ ረሐብተኛ አያካትትም፡፡ የግልና የመንግስት ሠራተኞች ለስሙ በየወሩ ደሞዝ ቢያገኙም ለመሠረታዊ ፍጆታ የሚውሉ ምርቶች ዋጋ ከአቅማቸው በላይ ንሯል፡፡ በዚህም የተነሳ የከተማው ሕዝብ በድርቅ ከተጎዳው ከገጠሩ ሕዝብ ባልተናነሰ ሁኔታ ለከፍተኛ አደጋ የተጋለጠ በመሆኑ ተደብቆ ያለው ረሐብ መጋረጃ ተገልጦ ተጠቂዎችን የሚታደጉ ግብረሰናይ ድርጅቶችን እይታና ትኩረት ይሻል፡፡ ይህ ካልሆነ ልክ እንደ ገጠሩ ድርቅ ፖለቲካ የፈጠረው የከተማው ችጋር እጅግ አስከፊ ውጤት ሊያስከትል ይችላል፡፡

## ሐ)አገዛዙ ምን እያደረገ ነው

አገዛዙ ምን እያደረገ እንደሆነ በቅጡ ለመረዳት የመለስና እኩይ የሥልጣን ተጋሪዎቹን አላማ ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ መለስ በሰው ስቃይና ሰቆቃ የሚደሰት የበሽተኛ አዕምሮ ባለቤት ከመሆኑም ሌላ እራሱንና ሥርወ መንግስቱን ለሚቀጥለው ሺህ አመት በሥልጣን ማቆየት ነው አላማው፡፡ ሥልጣን ማረጋገጫውና በሽተኛ አእምሮውን ለማዝናናት ለኢትዮጵያ ህዝብ የሰነቀው ርዕይ አንገቱን ደፍቶ እንዲኖርና ያላንዳች ጥያቄ እንዲገዛ ነው፡፡ ለዚህም በድህነትና በችጋር ቀፍድዶ ከማኖር የተሻለ አማራጭ አላገኘም፡፡

ሰርቶ ከከበረ ይጋፋኛል፤ አንድነቱ ከጠነከረ ይጋፈጠኛል ብሎ የሚሰጋው ዲያብሎሳዊ አዕምሮ ሕዝብን በከልል በረት ውስጥ አፍኖ፤ በከፋም ሆነ በደግ እንዳይተጋገዝና እንዳይተባበር ከፋፍሎ በተለያየ ምክንያት እርስ በርሱ ማናቆር ነው ለዚህ ህዝብ የሰነቀው ስልት፡፡ መለስ በሥልጣን እስካለ ሠርተን እንከብራለን፤ ከችግርና ከመከራ እንገላገላለን ብሎ ማሰብ የ"ላም አለኝ በሰማይ" ምኞት ነው፡፡ በመሆኑም የመንግስት ተብዬው የመለስ ቡድን ጉዳዩ ብሎ የያዘው ተግባር የኢትዮጵያውንን ችግር መታደግ ሳይሆን ማባባስ ነው፡፡

ድርቅ አብዛኛውን የአገሪተዋን ክፍል እያጠቃ፤ ባለፉት ሦስት አመታት እዚህ ግባ የሚባል ምርት አለመገኘቱ እየታወቀ "ችግሩ መጠነኛ በመሆኑ ካስመዘገብነው ከፍተኛ እድገት አንፃር ከኛ ቁጥጥር ውጪ አይሆንም፤ እርዳታም አያስፈልገንም" እያለ በአደባባይ ከመጮህ አልፎ "እርዳታ ሰጭ ድርጅቶች ጉዳዩን የሚያካብዱት ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ እንጂ ለህዝብ አስበው አይደለም" እያለ ይከራከራል፡፡

የምንኮራበት ባይሆንም ሕዝብ ችግር ሲደርስበት ያለውን አከፋፍሎ፤ እርዳታ ለማሰባሰብ እንዲያስችለው የተቸገረ እንዳለ ወይም ሊኖር እንደሚችል ገምግሞ፤ ምን ያህል እንደሆነ ገምቶ፤ ችግረኛውን ለመታደግ ምንና ምን ያህል እንደሚያስፈልግ አስልቶ በጎ አድራጊ ድርጅቶችንና የውጭ መንግስታት ተወካዮች ጋብዞ እርዳታ እንዲያደርጉ ይማጸን የነበረውን የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽንን ከማፍረስ ባላነሰ ሁኔታ አሽመድምዶታል፡፡ በመሆኑም በችግረኛው ሕዝብና በረጂዎች መካከል ሆኖ እርዳታ የሚያሰባስብ፤ በተለይም በመንግስት ስም ለችግር መውጫ እርዳታ እንዲሰበሰብ የሚማፀን ክብደትና ተአማኒነት ያለው ድርጅት የለም ለማለት ይቻላል፡፡

እስከዛሬ ከችግር ይታደጉን የነበሩትን መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን (መያዶችን) "ሕዝብ ታሳድሙብኛላችሁ፤ ለውጪ የዜና አውታሮችና ለመንግስቶቻችሁ ታሳብቁብኛላችሁ፡፡ ስለዚህም ኢትዮጵያ ውስጥ እንድትሰሩ አልፈቅድላችሁም» ብሎ ከአገር እያስወጣ ነው፡፡

## መ) አለም ምን እያደረገ ነው፡፡

ደግነቱ አለም መለስን እየታዘበ ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች፤ የተባበሩት መንግስታት አካላት፤ እንዲሁም ወዳጅ መንግስታት በኢትዮጵያ ላይ ያንዣበበውን አደጋ አስመልክተው በየበኩላቸው አስፋላጊ መስሎ የሚታያቸውን እርምጃ እየወሰዱ ነው፡፡

አገር በቀልና የውጭ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ያሰባሰቡትን መረጃ መሰረት በማድረግ ለመላው አለም አቤቱታ እያቀረቡ ነው፡፡ አገሪተዋን የከፋ ችግር ሊያጋጥማት እንደሚችል ምልክት መታየት የጀመረው የዛሬ ሶስት አመት ገደማ መሆኑን፤ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የተጠቂው ህዝብ መጠን በቋሚነት ከታወቀው 6 ሚሊዮን በየመቱ እያሻቀበ መሄዱን፤ አምና ወደ 15 ሚሊዮን ከፍ ማለቱን፤ እስከአሁን ባላቸው ጊዜአዊ መረጃ ችግሩ እጅግ ያጠቃቸው 20 ሚሊዮን እንደሆኑ፤ ከዚህ የማያንሰው በከፍተኛ ስጋት ላይ እንደሚገኝ ለአለም ህዝብ አቅርበዋል፡፡ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡

ከዚህም አልፈው ችግሩን ለመግታትና ሕይወት ለማዳን ከአሁኑ ርብርብ ካልተደረገ አደጋው ከ1977 የባሰ እንደሚሆን አስቀድመው እያሳሰቡ ነው፡፡ በዚያን አመት የደርግ መንግስት ችግሩን በማናናቅ የፓርቲ ምስረታ ድግሱን ሲያሟሙቅ ወደ አንድ ሚሊዮን የሚጠጋ ህዝብ እንዳለቀ አስታውሰው ካሁኑ እርዳታው መፍሰስ ካልጀመረና የወያኔው መንግስት ተገዶ እርዳታው ለሕዝብ በአስቸኳይ ሊያቀርብ የሚችልበትን ሁኔታ ካልተፈጠረ ካሁኑ የችግሩ ሰለባ እንደሆነ ከተገመተውና አስቸኳይ እርዳታ ከሚያስፈልገው 20 ሚሊዮን ሕዝብ ቢያንስ ቢያንስ ግማሹ ሊሞት እንደሚችል እየወተወቱ ነው፡፡

የተባበሩት መንግስታት የሕጻናት አድን ድርጅት (ዩኒሴፍ) ጥቅምት 4 ቀን ባወጣው መግለጫ በምስራቅ አፍሪቃ ወደ 5 ሚሊዮን የሚሆኑ ጎፃናት ለአደጋ መጋለጣቸውን ገልፆ ከዚህ ውስጥ ከሶስት ሚሊዮን የሚበልጡት ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን ገምቷል፡፡ ለችግር ከተጋለጡት ውስጥ ከ 500,000 የማያንሱቱ እጅግ የተጎዱ መሆናቸውን፤ የተቸገሩትን ለመርዳት ከዛሬ ሁለት አመት በፊት ከተደራጁ 500 የመመገቢያና የመርጃ ጣቢያዎች በተጨማሪ ሌሎች 2700 መደራጀታቸውን ገልጿል፡፡ አመላካች ምልክቶች እንደሚጠቁሙት ከሆነ ችግሩ ከቁጥር ውጪ ሊሆን እንደሚችል ድርጅቱ ይፋ አድርጎ፤ ለጋሽ አገራት ይህን ችግረኛ ሕዝብ እንዲታደጉ ተማፅኖ አቅርቧል፡፡ **ክፍል 2 በሚቀጥለው ሳምንት ይርባል**

## ፋሽስቱ መለስ ዜናዊ ለከፍተኛ ህክምና ቤልጄዬም . . .

ከገጽ 1 የዞረ

ከዚህም በተጨማሪ የህክምና ባለሙያ የሆነውና ነዋሪነቱ በሰሜን አሜሪካ የሆነ የብርሃኔ ገብረ ክርስቶስ ወንድም ዶ/ር ኤፍሬም ገ/ክርስቶስ ለሙያ አማካርነት ተጠርቶ አብሮት ሰንብቶ እንደተመለሰ ምንጮቻችን ገልጸዋል።

በዚህች አጭር ጊዜ ውስጥ በድጋሚ ለከፍተኛ ህክምና ወደውጭ የተጓዘው ፋሽስቱ መለስ ዜናዊ ተኝቶ በታከመበት ሆስፒታል የሚሰሩ ሃኪሞች፤ የሆስፒታሉ ሠራተኞችና በሆስፒታሉ የሚታከሙ ህሙማን ማመን እስኪያቅታቸው ድረስ ከፍተኛ ጥበቃ ይደረግለት እንደነበር ወደ ሆስፒታሉ ተጉዞ የነበረ የግንቦት 7 ዘጋቢ አረጋገጦአል። በአውሮፓ የወያኔ አምባሳደር የሆነውና ከመለስ ዜናዊ ጋር ልዩ የጥቅም ትስሥር አለው የሚባለው ብርሃኔ ገብረክርስቶስም እንደ ጸጥታ ሰራተኛ አለቃው ከተኛበት ክፍል እንደማይርቅ እንዲያውም ምግብ ከማመላለስ አልፎ በበሽተኛ አለቃውና በሃኪሞች መካከል ተላላኪ በመሆን እዚያው ሆስፒታል ይውል ያድር እንደነበር ታውቆአል።

መለስ ዜናዊ ለህክምና ቤልጅዬምን የመረጠበት ምክንያት ከብርሃኔ ገብረክርስቶስ ጋር ባለው ልዩ ቅርበት እንደሆነና ሶስቱም ልጆቹ ዝግ የትምህርት ቤት እረፍት ጊዜያቸውን ከርሱ ቤት እንደሚያሳልፉ ይታወቃል።

ይህ በዚህ እንዳለ የመለስ ዜናዊ ወደ ቤልጄዬም ለህክምና መመላለስን ለተቃዋሚዎች መረጃ ሊሰጡ ይችላሉ በሚል ፍራቻ ወያኔ በበልጅዬም የኤምባሲው ጽ/ቤት አካባቢ የሚሰሩትን የሌሎች ብሄረሰብ አባላትን አንድ ባንድ በማባረር ታማኝ ሊሆኑ ይችላሉ ብሎ በሚገምታቸው የትግራይ ተወላጆች መተካቱንና እነዚህኑ ታማኝ ናቸው ያላቸውንም ቢሆን የመለስን ወደ ስፍራው መምጣት እንዳያውቁ ጥብቅ ሚስጥር እንደሚያደርግባቸው ለማወቅ ተችሎአል።

ቀደም ሲል በኤምባሲው ውስጥ ይሰሩ የነበሩ ኢትዮጵያዊያን የፕሮቶኮል ሾፈሮች በሙሉ እንደተባረሩና በውጪ አገር ዘጎች እንደተተኩም ዘጋቢያችን አያይዞ ገልጾአል።

ድህረ ምርጫ 97 በአዲስ አበባ እና በሌሎች የአገሪቱ ክፍሎች ሰላማዊ ሰልፈኞች ላይ ፋሽስታዊ ጭፍጨፋ እንዲካሄድ ቀጥተኛ የሆነ አመራር በመስጠት፡ ከዚያም በኦጋዴን ወገኖቻችን ላይና በጎረቤት ሱማሌ ለተካሄደው የጦር ወንጀል ተጠያቂ የሆነው መለስ ዜናዊ በሰራቸው ወንጀሎች ብዛት ተጠያቂነቱ እየጎላ በመምጣቱ ከከፍተኛ ጭንቀት የመነጨ የስነልቦናና የአካል በሽታ ውስጥ እንደወደቀ ለርሱ ቅርበት ባላቸው ሰዎች አካባቢ በሰፊው ይነገራል።

የንጹሀንን ደም በግፍ ያፈሰሱ ሰዎች መጨረሻቸው እንደማያምር በርካታ የታሪክ ማስረጃዎች የሚያሳዩ ሲሆን፣ የመለስ ዜናዊም መጨረሻ ከእነዚህ ግፈኞች መካከል እንደሚሆን የሚናገሩ በርካታ ናቸው። በአለም ላይ በግፍ አገዛዛቸው ከሚታወቁት ሰዎች መካከል የናዚ አባላት የነበሩት ሂትለር፣ ኢክማን ፣ ሀንስፍራንክ ፣ ጎብልስ፣ ጎሪንግ፣ አመን ጎዝ፣ ሄድሪክ፣ ሂሚለር፣ ሩዶልፍ ሁስና ካርል ኮች በሰዎች እጅ የተገደሉ ወይም ራሳቸውን ያጠፉ መሆናቸው ሲታወቅ፣ የጣሊያኑ ሙሶሊኒ፣ የሮሜኒያው ቻውቼስኮና የኢራቁ ሳዳም ሁሴን እንዲሁ ባሰቃቂ ሁኔታ የተገደሉ ናቸው።

## 2ሺ የዩኒቨርስቲ መምህራን . . . ከገጽ 1 የዞረ

ተማሪዎች፣ ራሳቸውን እንኳ በትክክል ለመግለጽ አይችሉም የሚሉት ኤክስፐርቱ፣ የወያኔ የትምህርት ፖሊሲ ውጤት አለማምጣቱ በባለሙያዎች ተደጋግሞ የተገለጸ ቢሆንም፣ የወያኔ ባለስልጣናት ግን ለባለሙያተኞች አስተያየት መለስ ከመስጠትና የትምህርት ጥራትን ለመጠበቅ ከመስራት ይልቅ የተማሪውን ቁጥር ማብዛቱ ላይ ትኩረት አድርገዋልም ሲሉ አስረድተዋል።

በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ይሰሩ የነበሩ ነባር መምህራን በፖለቲካ አቋማቸው ምክንያት በመባረራቸው፣ አንዳንዶችም የወያኔን የትምህርት ፖሊሲ በመቃወም አገር ጥለው በመሰደዳቸው ወይም በተለያዩ የግል ድርጅቶች ውስጥ ተቀጥረው በመስራታቸው፣ በዩኒቨርስቲዎች ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የባለሙያ እጥረት መከሰቱን ኤክስፐርቱ ገልጸዋል።

በተያያዘ ዜናም በአዲስ አባባ ዩኒቨርሰቲ የሚገኙ ተማሪዎች የመብት ጥያቄ ለማንሳት በማይችሉበት ደረጃ መገኘታቸውን አንድ የዩኒቨርሰቲ ተማሪ ገለጸ።

ስሙ እንዳይገለጽ የፈለገ የሶስተኛ አመት የህግ ተማሪ ለግንቦት7 ዘጋቢ እንደተናገረው፣ በዩኒቨርሰቲው ውስጥ የተመደቡት ተማሪዎች አብዛኞቹ የወያኔ አባሎች በመሆናቸው በአገራቸው ውስጥ ያለውን የፍትህ እጦት፣ የመብት አፈናና የኢኮኖሚ ድቀት ተቃውመው ለመነሳት አልቻሉም። በዩኒቨርስቲው ውስጥ ካለው የተማሪዎች ቁጥር ይልቅ የሰላዮች ቁጥር እንደሚበዛ የሚናገረው የህግ ተማሪ፣ ፖሊቲካ ነክ ጉዳዮችን አንስቶ መወያየት ከዩኒቨርስቲ መባረርን ብቻ ሳይሆን እስራትና ሞትን ያስከትላል ብሏል። አገዛዙን የሚቃወሙ ተማሪዎችም ቢሆኑ በግል ስሜታቸውን ከመግለጽ ውጭ፣ ሌሎችን ተማሪዎች አስተባብረው ተቃውሞዋቸውን ለማሰማት በማይችሉበት ደረጃ መገኘታቸውን ቁጭት በተቀላቀለበት ስሜት ገልጿል። እንድርያስ እሸቴ የትምህርት ጥራትና የተማሪዎችን መብቶች ለማስከበር ከሚሰራው ስራ ይልቅ፣ አብዛኛውን ጊዜውን የሚያጠፋው ከዩኒቨርሰቲው የደህንነት አባሎች ጋር ተማሪውን እንዴት አፍኖ እንደሚይዝ በመወያየት ነው ሲልም ተናግሯል።

## በኢትዮጵያ የተከሰተው ረሀብ ከፍተኛ . . . ከገጽ 1 የዞረ

ቁጥር በየጊዜው አሳንሶ እንደሚያቀርብ ይታወቃል። በያዝነው አመትም የአምባገነኑ አገዛዝ በረሀብ የተጠቃውን ወገን ቁጥር በትክክል ከመናገር ይልቅ፣ ከእርዳታ ድርጅቶች ጋር መጣላትን እንደመረጠ ፋሽስቱ መለስ ዜናዊ በፓርላማው ተገኝቶ ከሰጠው መልስ ለመረዳት ይቻላል። በባለፈው ሳምንት የፓርላማ ንግግር ዘረኛው መለስ ዜናዊ "በኢትዮጵያ የተራበው ህዝብ ቁጥር ተጋኖ ቀርቡዋል፣ የአለማቀፍ የእርዳታ ድርጅቶችም ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ የኢትዮጵያን የረሀብተኛ ቁጥር አጋነው እያቀረቡ ነው" የሚል ወቀሳ አሰምቶ ነበር። የአለማቀፍ ድርጅቶች በበኩላቸው "የመለስ አገዛዝ ለፖለቲካ ፍጆታ ሲል የረሀብተኛውን ቁጥር አሳንሷል፣ በኢትዮጵያ የተራበው ቁጥር ከ13 ሚሊዮን ህዝብ በላይ ነው" የሚል መልስ በመስጠት ላይ ናቸው።

በአለማቀፍ የእርዳታ ድርጅት ተቋም ላይ የሚሰሩ አንድ ኢትዮጵያዊ ረሀቡን አስመልክቶ ከግንቦት 7 ድምጽ ለቀረበላቸው ጥያቄ ሲመልሱ " በርግጥም በኢትዮጵያ የተከሰተው ረሀብ ከመቼውም ጊዜ የከፋ ነው። የመለስ አገዛዝ የረሀብተኛውን ቁጥር ሆን ብሎ መቀነሱ ይታወቃል። የአለማቀፍ ድርጅቶችም የፖለቲካ ንትርኩን በመፍራት ቁጥሩን አሳንሰው በመናገር ላይ ናቸው። በአጠቃላይ በኢትዮጵያ የተራበው ህዝብ ቁጥር ከ15 ሚሊዮን በላይ ነው። ይህንንም አህዝ በቅርቡ ትሰሙታላችሁ። መለስ ማጠፊያው ሲያጥረው እውነቱን ማውጣቱ አይቀርም" ብለዋል።

የወየኔ አገዛዝ ለምን የረሀብተኛውን ቁጥር ለመቀነስ ፈለገ ተብለው ለተጠየቁት ሲመልሱ ደግሞ " በመጀመሪያ ከአምባገነን መንግስታት ባህሪ አንዱ ረሀብ በመጣ ጊዜ የረሀብተኛውን ቁጥር ቀንሶ መናገር ነው። የመለስ አገዛዝ ሌት ተቀን የሚያስበው የረሀቡ ቁጥር በስልጣን እድሜው ላይ ስለሚኖረው ተጽኖ ነው እንጅ በረሀብ ስለሚሞተው የኢትዮጵያ ህዝብ አይደለም። የአጼ ሀይለስላሴና የመንግስቱን ሀይለማሪያም አገዛዞች የወደቁት ከረሀብ ጋር በተያያዘ ነው። የመለስ አገዛዝ እጣ ፋንታም ከዚህ እንደማይዘል ያውቀዋል፤ ስለዚህ ሁሌም በአገሩ ረሀብ እንደሌለ፣ ቢኖርም የተራበው ህዝብ ቁጥር ትንሽ እንደሆነ የሚያሳይ ሪፖርት ያቀርባል" ይላሉ።

ባለሙያው በመጨረሻም " አብዛኛው ህዝብ በቀን አንድ ዳቦ መብላት የማይችልበት ደረጃ ላይ ድርሷል። በቀን አንድ ዳቦ በልተው የሚኖሩት ዜጎች ቁጥር ቢደመር፣ በኢትዮጵያ አገሩ በሙሉ ትረቧል ማለት ይቻላል። ይህም የወያኔ ግብርና መር ፖሊሲ ፍሬ አልባ መሆኑን የሚያሳይ ነው። አሁን የኢትዮጵያ ህዝብ የመጨረሻውን ለውጥ የሚጠይቅበት ጊዜ ላይ የደረስን ይመስለኛል" ሲሉ አጠቃለዋል።

የወያኔ አገዛዝ በታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ከፍተኛ የሆነ አለማቀፍ እርዳታ የሚያገኝ ቢሆንም፣ ላገዘዙ ቀረቤታ ያላቸው ጥቂት ግለሰቦች ካልሆኑ በስተቀር አብዛኛው ህዝብ የበይ ተመልካቸው መሆኑ ይታወቃል።

ግንቦት 7 የኢትዮጵያን ህዝብ ከረሀብ፣ ከችጋር፣ ከእርዛትና ከፍትህ እጦት ለማላቀቅ የሚቻለው የበሰበሰውን የወያኔን አገዛዝ ሙሉ በሙሉ በማፈራረስ ብቻ መሆኑን በማመን፣ ከፍተኛ ትግል እያደረገ መሆኑ ይታወቃል።

## ህዝቡ ለወያኔ የምርጫ ፕሮፓጋንዳ . . . ከገጽ 1 የዞረ

ወያኔ መጭውን የይስሙላ ምርጫ አስመልክቶ ሁለት የሚምታቱ አቋሞችን እያንጸባረቀ እንደሚገኝ የገለጹት ደግሞ በአዲስ ከተማ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የጂኦግራፊ መምህር ሲሆኑ፣ እነዚህን የሚምታቱ አቋሞችን ሲገልጹም ወያኔ "በአንድ በኩል አሁን ያሉትን ተቃዋሚዎች መዳከም አይቶ አልሸነፍም የሚል ስሜት እያደረበት በመምጣቱ ምርጫውን ነጻ ለማድረግና የተበላሸ ምስሉን ለመቀየር እየሞከረ ይመስላል፤ በሌላ በኩል ደግሞ የግንቦት 97ቱ ምርጫ ታሪክ ድንገት ሲታወሰው ለማመን የሚያስቸግሩ እርምጃዎችን በህዝቡና በተቃዋሚዎች ላይ ሲወስድ ይታያል" ብለዋል። ህዝቡ የወያኔን እውነተኛ ባህሪ ጠንቅቆ በማወቁ ለወያኔ ቅስቀሳ ቦታ እንደማይሰጠው የሚናገሩት መምህሩ፣ መጪው ምርጫ የይስሙላ ምርጫ እንደሚሆንም ተናግረዋል።

በሌላ በኩል ደግሞ ወያኔ በሀይል ካልሆነ በምርጫ አይወርድም የሚለው የህዝብ እምነት እየጨመረ መምጣቱን ዘጋቢያችን ገልጿል። ህዝቡ በአሁኑ ጊዜ በስፋት የሚከታተለው የነጻ አውጭዎችን የሬዲዮ ጣቢያዎች መሆኑን የገለጸው ዘጋቢያችን፣ ወያኔም ይህንን በመረዳቱ ሰሞኑን በነጻ አውጭ ድርጅቶች ላይ የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ መክፈቱን ላብነት ጠቅሷል። ሰሞኑን የወያኔ የመገናኛ ብዙሀን ከቋራና ከወልቃይት ገንዘብ ተከፍሎአቸው የቀረቡ ነዋሪዎችን በማናገር በአርበኞች ግምባር ላይ ከፍተኛ የሆነ ቅስቀሳ በማካሄድ ላይ ሲሆን፣ ህዝቡ ግን ይህን የወያኔን ቅሰቀሳ ገልብጦ በመስማት የአርበኞች ግምባርን እንቅስቀሴ በአንክሮ በመከታተል ላይ ነው።

የግንቦት 7 ትን ሬዲዮ የሚከታተለውም ህዝብ ቁጥር በየጊዘው እየጨመረ መምጣቱን የገለጸው ዘጋቢያችን፣ ህዝቡ በንቅናቄው ላይ ያለው አመኔታ እጅግ እየጨመረ መሆኑንም ገልጿል።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**

**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

**በ 7530 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ** እና **በ 9610 KHZ በ 31 ሜትር ባንድ** ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዣችንን እናቀርባለን g7radio@ginbot7.org ወይም በስልክ ቁጥር 0044- 203-286- 9661